Immigration
Advice
Authority





# የኢሚግሬሽን ምክር ይሻሉ? IAA (የኢሚግሬሽን ማማከር ባለሥልጣን) ሊረዳዎ ዝግጁ ነው።

ማንኛውም የኢሚግሬሽን ማማከር አገልግሎት የሚያቀርብ አካል በአግባቡ ቁጥጥር ይደረግበታል። **Immigration Advice Authority (IAA) (የኢሚግሬሽን ማማከር ባለሥልጣን)** ለኢሚግሬሽን አማካሪዎች Code of Standards (የደረጃዎች ኮድ) ያዘጋጃል፣ እንዲሁም የተፈጠሩ ችግሮች ካሉ እርስዎን በመወከል በቅሬታዎ ዙሪያ ምርመራ ሊያከናውን ይችላል።

ሊያምኑት የሚችሉት የኢሚግሬሽን ምክር ማግኘትዎን ለማረጋገጥ፣ አማካሪዎ IAA (የኢሚግሬሽን ማማከር ባለሥልጣን) ላይ የተመዘገበ መሆኑን ያረጋግጡ፣ ወይምፈቃድ የተሰጠው አማካሪ በእኛ በኩል ያፈላል።

## በIAA (የኢሚግሬሽን ማማከር ባለሥልጣን) የተመዘገበ አማካሪ

gov.uk/iaa ን በመጎብኘት የተመዘገበ የኢሚግሬሽን አማካሪ ማግኘት ይችላሉ

## Immigration Advice Authority (IAA) (የኢሚግሬሽን ማማከር አገልግሎት ባለሥልጣን) ማነው?

IAA (የኢሚግሬሽን ማማከር ባለሥልጣን) የኢሚግሬሽን ማማከር አገልግሎት አቅራቢዎችን የሚቆጣጠር እና በኢሚግሬሽን ማማከር ዘርፍ ምርጥ ተሞክሮዎች እንዲተገበሩ የሚሰራ ድርጅት ነው። እኛ ዘንድ ለመመዝገብ፣ አንድ አማካሪ Code of Standards (የደረጃዎች ኮድ) ችንን ማሟላቱን እና ያንንም እንዳሟላ የሚቀጥል መሆኑን ማረጋገጥ አለበት።

በአግባቡ ፈቃድ ሳያገኙ የኢሚግሬሽን ምክር አገልግሎት መስጠት UK (ዩኬ) ውስጥ ሕገወጥ ነው። ይኸን የሚያደርጉ ተጋላጭ ሰዎችን አደጋ ላይ ከመጣላቸውም በላይ የኢሚግሬሽን ሥርዓቱንም ይጐዳሉ። IAA (የኢሚግሬሽን ማማከር ባለሥልጣን) ሕግ የሚጥሱ አማካሪዎች ላይ እርምጃ የመውሰድ ሥልጣን አለው።



## በአንድ አማካሪ ላይ የሚቀርብ ቅሬታ

መጥፎ ተሞክሮ አጋጥሞዎ ከሆነ፣ እንዲነግሩን እና ነገሮችን ለማስተካከል እንድንረዳዎ እንፈልጋለን። ስለሚከተሉት ጉዳዮች ቅሬታዎን ለIAA (የኢሚግሬሽን ማማከር ባለሥልጣን) ማቅረብ ይችላሉ፦

- በIAA (የኢሚግሬሽን ማማከር ባለሥልጣን) ከተመዘገበ አማካሪ ደረጃውን ያልጠበቀ አገልግሎት አግኝተው ከሆነ፣ ለምሳሌ የተሳሳተ መረጃ ከተሰጠዎ፣ ከተገቢው በላይ ክፍያ ከተጠየቁ፣ ብልሹ የደንበኛ አገልግሎት ካጋጠመዎ፣ ጥሩ ያልሆነ ምክር ከሰጡዎ ወይም መልስ የማይሰጡዎ ከሆነ
- ካልተመዘገበ አማካሪ የኢሚግሬሽን ምክር አግኝተው ከሆነ

እርስዎን በመወከል ሌላ አካል፣ ለምሳሌ ጓደኛ፣ ረዳት ወይም ፈቃደኛ ድርጅት፣ ሰው ቅሬታ እንዲያቀርብልዎ ማድረግ ይችላሉ።

ድር ጣቢያችንን ለመጎብኘት ይህን ስካን ያድርጉ

## እኛን እዴት ማግኘት እንደሚችሉ

ቅሬታ ለማቅረብ፣ ወይም አጠቃላይ ስጋትዎን ለመግለጽ፣ IAAን (የኢሚግሬሽን ማማከር ባለሥልጣን) ለማግኘት በርካታ መንገዶች አሉ፦

ወደ gov.uk/iaa ይሂዱ

ኢሜይል info@immigrationadviceauthority.gov.uk